# በምክር ቤቱ 9ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ እና 11ኛው ንግድ ትርዒት ላይ ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጠ

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት 9ኛውን የምክር ቤቱ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ እና 11ኛውን ኢትዮ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት አስመልክቶ ጥቅምት 20 ቀን 2011 ዓ.ም. በምክር ቤቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ፡፡

መግለጫውን የሰጡት የምክር ቤቱ ምክትል ፕሬዚደንት አቶ አሰፋ ገብረ ስላሴና የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ አቶ እንዳልካቸው ስሜ እንደተናገሩት የፊታችን ጥቅምት 26 ቀን 2011 ዓ.ም. የሚካሄደው 9ኛው የምክር ቤቱ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ከሚያነሳቸው ዋነኛ አጀንዳዎች መካከል የምክር ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/95 እና ሌሎች መመሪያዎችን አስመልክቶ እየተደረገ ያለው ማሻሻያ ሰፊ ውይይት እንደሚያስተናግድ ይጠበቃል፡፡

ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/95 ከተቋቋመ 16 ዓመታትን ማስቆጠሩንና ሲፀድቅም ከነችግሩ ነበር ያሉት የምክር ቤቱ ምክትል ፕሬዚደንት አቶ አሰፋ ገብረ ስላሴ የግሉ ዘርፍ የሚወከልበት ምክር ቤት በሚገባ እንዲደራጅ የማቋቋሚያ አዋጁን ጨምሮ አሠራሮችና መመሪያዎች መሻሻላቸው የሚያጠያይቅ አይደለም ብለዋል፡፡

ጠንካራ የግል ዘርፍ መፍጠር ካልተቻለ የተጀመረውን ልማት ማስቀጠል አስቸጋሪ ነው ያሉት የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ አቶ እንዳልካቸው ስሜ በበኩላቸው እንደተናገሩት መንግስት ፕራይቬታይዜሽንን በተመለከተ እየወሰደ ያለው እርምጃም ለግሉ ዘርፍ የሰጠውን ትኩረት ያሳያል ብለዋል፡፡

9ኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የ2010 በጀት ዓመት የሥራ አፈጻጸምና ኦዲት ሪፖርት እንደሚያደምጥም ይታወቃል፡፡

በተያያዘ ዜና የምክር ቤቱ ኃላፊዎች 11ኛውን ኢትዮ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት በተመለከተም መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

ምክር ቤቱ በየመቱ ‹‹ኢትዮ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት››ን




በስተቀኝ፡- የምክር ቤቱ ም/ፕሬዚደንት እና በስተግራ፡- የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ

‹‹የኢትዮጵያን ይግዙ›› በሚል መሪ ቃል እንደሚያካሂድ የገለጹት ኃላፊዎቹ የንግድ ትርዒቱ ዓላማ የሀገሪቱን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ እና በሀገሪቱ ያለውን የኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ በማስተዋወቅ ለሀገር ውስጥ ምርት የገበያ ዕድል የሚፈጠርበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሆነ በመግለጫቸው አስታውሰዋል፡፡

ኢትዮጵያ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ከአፍሪካ ቀዳሚ ከሚባሉት ተርታ በመሰለፏ የንግድ ትርዒቱ በኢትዮጵያ ኢንቨስት ማድረግ በተለይ በአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጠና ውስጥ ሳቢ እንደሚሆን ማሳያ ይሆናልም ብለዋል ኃላፊዎቹ በመግለጫቸው፡፡

የዘንድሮው 11ኛው የንግድ ትርዒት የተለየ አጀንዳ ባይኖረውም ብዙ የማናውቃቸው የሀገር ውስጥ ምርቶች ያሉ በመሆናቸው እነሱን ልናስተዋውቅበት እንደምንችል ኃላፊዎቹ እምነታቸውን ገልጸዋል፡፡

ከሀሙስ ጥቅምት 22 -26 ቀን 2011 ዓ.ም. የሚቆየው 11ኛው ኢትዮ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ወ/ሮ ፈትለወርቅ ገብረ እግዚአብሄርን ጨምሮ ሌሎች የመንግሥት ኃላፊዎችና አምባሳደሮች በተገኙበት ከ13 ሀገሮች የተውጣጡ 39 ያህል እና 200 ያህል የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ምርቶቻቸውን እና አገልግሎቶቻቸውን ያስተዋውቃሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በመጨረሻም ኃላፊዎቹ ከጋዜጠኞች ለተሰነዘሩ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል፡፡



## የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንትና ቢዝነስ ማስፋፋት ፕሮገራም ለጄን (ህንድ) ዓለም አቀፍ ንግድ ድርጅት የቢዝነስ ልዑክ ተዘጋጀ



የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት፣ ከጄን(ህንድ) ዓለም አቀፍ ንግድ ድርጅት እና ከኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመሆን ለጄን(ህንድ) ዓለም አቀፍ ንግድ ድርጅት የቢዝነስ ልዑክ ያዘጋጀው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንትና ቢዝነስ ማስፋፋት ፕሮገራም ከጥቅምት 14-15 ቀን 2011 ዓ.ም. በድሪም ላይነር ሆቴል ተካሄደ፡፡

ስለ ኢትዮጵያና ህንድ የቢዝነስ ግንኙነት፣ በኢትዮጵያ ስላሉ የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎች እና ማበረታቻዎች እንዲሁም በርካታ ተመሳሳይ ርእሶችን አስመልክቶ ለጄን(ህንድ) ዓለም አቀፍ ንግድ ድርጅት የቢዝነስ ልዑክ ገለፃ ተደርጎላቸዋል፡፡

በኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቢዝነስ ዲፕሎማሲ ጀነራል ዳሬክተር አቶ መስፍን ገ/ማርያም በእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግራቸው እንደገለፁት ፎረሙ በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የኢንቨስትመንትና የንግድ ልውውጥ የበለጠ እንዲስፋፋ እድል ይፈጥራል፡፡ ኢትዮጵያ በተለይም በጨርቃጨርቅ፣ በመድሀኒት፣ በታዳሽ ሃይል፣ በግንባታና በአግሮ ፕሮሰሲንግ ላይ የሚሰማሩ የህንድ ባለሀብቶችና ስራ ፈጣሪዎችን ለመቀበል ከመቸውም በላይ ዝግጁ እንደሆነች አቶ መስፍን አክለዋል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የንግድና የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ቢንያም ምስግና በበኩላቸው እንደተናገሩት ኩነቱ በሁለቱ አገሮች ንገድ ማህበረሰብ መካከል የተመሰረተውን የሁለትዮሽ ግንኙነት የሚያጠናክር እና የቢዝነስ እድሎችንም ለማስፋፋት መንገድ የሚጠርግ ነው፡፡ አቶ ቢንያም ጨምረው እንደተናገሩት የህንድ ኩባንያዎች ከኢትዮጵያ ባለሀብቶች ጋር በመሆን በሀገሪቱ ውስጥ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ምክር ቤቱ ያበረታታል፡፡

በአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ በመድሃኒት ምርቶች፣ በግንባታ ቁሳቁስ፣ በትምህርት መሳሪያ አቅርቦት፣ በፕላስቲክ ምርቶች፣ በዘይት እህሎች፣ በሩዝና ስንዴ፣ በጥጥ፣ በብረታ ብረት፣ በጨርቃጨርቅ፣ በወረቀት፣ በሎጂስቲክ፣ በመማሪያ መፅሀፍት ህትመትና በኬሚካል ምርቶች ላይ የተሰማሩ ሰላሳ የህንድ ኩባንያዎች በተመሳሳይ ዘርፍ ከተሰማሩ ስድሳ የአትዮጵያ የግል ኩባንያዎች ጋር የአቻ ለአቻ ውይይት አካሂደዋል፡፡

የጄን(ህንድ) ዓለም አቀፍ ንግድ ድርጅት የቢዝነስ ልዑክ ከሚመለከታቸው የኢፌዲሪ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ከፍተኛ የመንግስት ሃላፊዎች ጋር በመገናኘት በሀገሪቱ የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎች እና ማበረታቻዎች ላይም ውይይት አካሂደዋል፡፡

## የኢትዮጵያ-ሆንግ ኮንግ የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስር ፎረም ተካሄደ






የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ የማህበራት ምክር ቤት ከሆንግ ኮንግ የንግድ ልማት ምክር ቤት እና ከቻይና ኢምባሲ ጋር በመተባበር ጥቅምት 8/2009 ዓ.ም. በሸራተን አዲስ ሆቴል የኢትዮጵያ -ሆንግ ኮንግ የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስር ፎረም አዘጋጀ፡፡

የፎረሙ አላማ በሁለቱ አገሮች ያለዉን የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ለማጠናከርና አዳዲስ የቢዝነስ ትስስሮችን ለመመስረት ነዉ፡፡

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ኢንጂነር መልአኩ እዘዘው በእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግራቸው እንደተናሩት ኢትዮጵያ ገበያ ተኮር የሆነ የኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ ነፃ የኢንቨስትመንት ህግ፣ ተስማሚ የቢዝነስ ምህዳር እና በርካታ ቁጥር ያላቸው የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎች ያሏት ሀገር በመሆኗ የሆንግ ኮንግ ኩባንያዎች በሀገሪቱ ኢንቨስት ለማድረግ ትክክለኛ ወቅት ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ወደ ሆንግ ኮንግ ያለው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራ የሁለቱን አገሮች እና የሁለቱን የንግድ ማህበረሰቦች መማገኛኘት ረገድ ሚና እንደሚጫወትም ፕሬዚደንቱ አክለው ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ፀኃፊ እንዳልካቸው ስሜም በኢትዮጵያ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ለሆንግ ኮንግ ባላሀብቶች ልዩ እድል ስለሆነ መዋዕለ ንዋያቸውን ሊያፈሱና ሊጠቀሙ ይገባል ብለዋል፡፡ በተመሳሳይም ሆንግ ኮንግ በተለይም በፋይናንስ ዘርፉ የዘመንች በመሆኗ የኢትዮጵያ የግል ኩባንያዎች ከዘርፉ ተጠቃሚ የሚሆኑበት እድል ሰፊ እንደሆነም ዋና ፀኃፊው ገልፀዋል፡፡

ስለ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እና እድሎቹ ከግሉ ዘርፍ ዕይታ አንፃር፣ በኢትዮጵያ ስላሉ የኢንቨስትመንት እድሎች እና ማበረታቻዎች፣ ስለ ኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርክ እድገት፣ ምቹ የሆኑ የቢዝነስ ከባቢ፣ እና ተዛማች ርእሶችን አስመልክቶ ለሆንግ ኮንግ ኩባንያዎች ሰፊ የፓወር ፖይንት ገለፃ ተደርጎላቸዋል፡፡

20 የሆንግ ኮንግ እና 200 የሚጠጉ የኢትዮጵያ የግል ኩባንያዎች እንዲሁም የሁለቱም ወገን ከፍተኛ የመንግስት ሀላፊዎች፣ በኩነቱ ላይ ተገኝተዋል፡፡

## የስሎቫኒያ የንግድ ልዑካን ከኢትዮጵያዊያን አቻዎቻቸው ጋር የአቻ ለአቻ ውይይት አካሄዱ



በስሎቬንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚኒስትሩ አማካሪ ሚስተር ደጃን ቪላዲክ የተመራው የስሎቬንያ የንግድ ልዑካን የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ኢንጂነር መላኩ እዘዘው እና ዋና ፀኃፊው እንዳልካቸው ስሜ በተገኙበት ከኢትዮጵያዊያን አቻዎቻቸው ጋር ጥቅምት 6 ቀን 2011ዓ.ም በቦርድ አዳራሽ የአቻ ለአቻ ውይይት አካሄዱ፡፡

የአቻ ለአቻ ውይይቱ በሁለቱ አገሮች ያለውን ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር እንደሚረዳ ተነግሯል፡፡

በኢትዮጵያ ስላሉ የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎች፣ በኢትዮጵያ እና በስሎቬንያ መካካል ስላለው ግንኙነት፣ የኤክስፖርት እና የኢምፖርት ምርቶች እና ተዛማጅ ጉዳዮችን አስመልክቶ የፓወር ፖይንት ገለፃ ተደርጓል፡፡

የንግድ ልዑካኑ በሀገራቸውም ሆነ በውጪ አገሮች በመድሀኒት ምርቶች፣ በአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ በኮንስትራክሽን፣ በብረታብረት፣ በእንጨት ስራ ማሽን እና በህትመት መስክ ተሰማርተው እየሰሩ ካሉ ቀዳሚ የስሎቬኒያ ባለሀብቶች መካከል እንደሆኑ ታውቋል፡፡

# Chamber Holds Press Conference on 9th GA and 11th Fair

Assefa G/Sillasie, V. President (V.P) and Endalkachew Sime, Secretary General (S.G.), of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA), delivered a press release on 30th of October 2018 to local media on the 9th General Assembly (G.A.) of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA) and on the 11th Ethio-Chamber International Trade



**V/President of ECCSA**

Fair.

According to the officials, the GA which is going to kick off on 5th of November 2018 will take the discussion about the revising of Chamber establishment proclamation no. 341/2003 and other regulations high on the agenda.

The V.P., who said the proclamation no. 341/2003, has gone through 16 solid years with no amendment and with all its limitations, underlined the fact that the need to revise it is no more contentious if there is a need to



**Secretary General of ECCSA**

have a well-organized institution that represents the private sector.

The S.G. who on his part said that if it is likely impossible to create strong private sector, it would be impossible to ensure the sustainability of the existing development. The reformative measure taken by the new cabinet of Ethiopian government on the privatization of the service sector shows the government's dedication to the growth of the private sector, he added.

The 9th GA will be expected to focus on issues of strengthening the private sector, said the S.G.

The GA will be expected to listen to the last year's performance and audit report.

In the meantime, the V.P. and the S.G. also delivered a press release about the 11th Ethio-Chamber International Trade Fair that is going to be held from November 1-5 2018.

The objective of Ethio-Chamber International Trade Fair which is held annually under the motto: "Buy Ethiopian" is mainly promoting Ethiopian products (goods), services, and industrial inputs to enhance competitiveness of the local industries and attracting investment, said the S.G.

As Ethiopia stands one of the first in Africa in attracting FDI, Ethio-Chamber Trade Fair plays a significant role in promoting Ethiopia's investment in AfCFTA, he added.

According to the officials, the 11th Ethio-Chamber International Trade Fair will be expected to promote new local products.

On the fair, about 39 companies from about 13 countries and about 200 local companies will be expected to exhibit their products.

Finally, the officials responded to questions raised from the journalists.



**Journalists in the press conference**

## Ethiopia Investment and Business Promotion Program to JITO Business Delegation Held.






Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA) jointly with Jian International Trade Organization (JITO) and Ethiopian Ministry of Foreign Affairs organized Ethiopia Investment and Business Promotion Program to JITO Business Delegation from October 24-25, 2018 at Dream Liner Hotel, Addis Ababa.

In his welcoming remarks, Mesfin G/Mariam, Business Diplomacy Director General of FDRE Ministry of Foreign Affairs said that the business forum would create opportunities to deepen investment and trade exchanges of the two countries. He also articulated Ethiopia is further ready to warmly welcome Indian investors and entrepreneurs to take advantage of the country's attractive incentives particularly in the manufacturing of textiles, and garments, pharmaceuticals, renewable energy, construction and agro-processing sectors.

Biniam Misgna, Director of Trade and Investment Promotion Directorate in ECCSA on his part said that the event is a means to expand business opportunities and deepen the already established bilateral relations between the two businesses. Biniam further said that the Chamber is pleased to encourage Indian companies to invest in Ethiopia by creating partnership with the local companies.

A power point presentation about Ethio-Indian Trade and Investment Relationship, Ethiopian trade and investment opportunities and incentives, and various related topics were presented to JITO Business Delegation.

Thirty nine JITO delegates engaged in the areas of pharmaceuticals, electrical products, food Processing, plastic products, paper Industry, agro-processing, oil seeds, rice and wheat, cotton, iron & steel, textile & apparels, chemical, construction, machinery & educational book publication, warehousing and logistics with 60 Ethiopian private companies have conducted a b2b meeting to do business in partnership and through joint venture.

It was learnt that the JITO business delegation also have had a one to one interaction with the concerned FDRE ministries and relevant government officials to discuss about the business opportunities and incentives.

## Ethiopia-Hong Kong Trade and Investment Networking Forum Organized

Ethiopia-Hong Kong Trade and Investment Networking Forum was organized by the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA) in Partnership with Hong Kong Trade Development Council (HKTDC) and Embassy of China to Ethiopian on October 18, 2018 at Sheraton Addis Hotel.






The forum was aimed at expanding the existing ties of trade and investment and creating new business networking of Ethiopia and Hong Kong.

During the briefing session, a power point presentation about Ethiopian Economy and its opportunities from the private sector's perspective, Ethiopian investment opportunities and incentives, enabling business environment in Ethiopia, industrial parks development in Ethiopia and related topics have been presented to the representatives of the Hong Kong companies.

In his welcoming remarks, Melaku Ezezew (Eng.), President of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA) stated that since Ethiopia has market oriented economy policy, liberal investment law, conducive business environment and immense number of trade and investment opportunities, it is the right time for Hong Kong companies to invest in it. The president further said that a

Cont. to page 7

## Slovenian Business Delegates hold B2B meeting with their Ethiopian



Slovenian business delegates headed by Dejan Vladic, Minister Counsellor of Slovenian Ministry of Foreign Affairs held b2b meeting with their Ethiopian counterparts with the presence of Melaku Ezezew (Eng.), President and Endalkachew Sime, Secretary General of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA) at ECCSA Board room on October 16, 2018.

It was said that the b2b between the business representatives of the two sides is expected to further enhance the economic relation of the two countries.

A power point presentation about Ethiopian trade and investment opportunities, trade turn over, export, import relationship between Ethiopia and Slovenia has been presented.

The delegates are among the top investors operating in their home town and overseas in the areas of pharmaceuticals, agro-processing, wood working machines, metallurgical equipment, construction and Printing.

## Ethiopia-Hong Cong ... (cont. from page 6

direct flight of Ethiopian Airlines to Hong Kong is also considered as one of the connecting forces between the two countries and businesses.






Endalkachew Sime, Secretary General of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA said that the manufacturing sector in Ethiopia is a unique opportunity which the Hong Kong companies should invest on and benefit from it and the Ethiopian companies also have a very big business opportunity in the service sector of Hong Kong especially the finance sector which is unexploited yet.

Over 20 Hong Kong companies, high ranking government officials from both countries and 200 representatives from Ethiopian private companies have attended the event.